የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር ዋኦመ/ተ.06.23/3/12
ቀን 28/07/2014

ለክቡር ዶ/ር ኢዮብ ተካልኝ

የኢፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ እና

የወለጋ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሰብሳቢ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፦ <u>የወለጋ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣</u>

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰውን ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 5 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 2 ገጽ የሂሣብ መግለጫዎች ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ወርቅነህ [illegible]
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለወለጋ ዩኒቨርሲቲ (ከ5 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ 20 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እና 7 ገጽ አባሪ ጋር)
  <u>ወለጋ፣</u>

የወለጋ ዩኒቨርሲቲ የ2013
የኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የወለጋ ዩኒቨርሲቲ
የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል::

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008(እንደተሻሻለ) ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና ሪፖርቶችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፤

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

1. ሁለት የመድሃኒትና ህክምና ዕቃ አቅራቢዎች በውላቸው መሰረት ባለማቅረባቸውና ከ118 እስከ 138 ቀን በማዘግየታቸው መድሃኒቶቹ በተፈለጉበት ጊዜ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ መስተጓጎልን ከመፍጠሩም በተጨማሪ ሳዘገዩበት ጊዜያት በህጉ መሰረት መሰብሰብ የነበረበት የጉዳት ካሳ ብር 205,631.10 ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
2. የግንባታ የመያዣ ሂሳብ አመዘጋገብና አያያዝ ስርዓት ላይ
   - ➢ ዩኒቨርሲቲዉ ለስፍለን ኢንጂነሪንግ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በዋናዉ ግቢ የሌክቸር ሆል /lecture whole/ እድሳት ስራ አከናዉኖ የመጨረሻ የሪቴንሽን/2.5%/ ብር 366,363.47 ተመላሽ ክፍያ ቢፈጽምም በተቋራጩ ተቀጽላ ሌጀር ኮድ 5061 0057 ብር 28,869.40 በክሬዲት የተያዘዉ በመሆኑ አለአግባብ የተከፋይ ሂሳብ ከፍ ያለ መሆኑ

➢ ለኤልናፍ ኢንጂነሪንግ በግንቢ ካምፓስ የኢንፍራስትራክቸር ቀሪ ግንባታ ስራ ላከናወነበት በ9ኛ ዙር የክፍያ የምስክር ወረቀት የብር 2,836,292.44 ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በቀረበዉ የክፍያ ምስክር ወረቀት መሰረት ተቋራጩ ለሪቴንሽን ያስያዘዉ ብር 1,096,937.96 ሲሆን በተቋራጩ የተቀጸላ ሌጀር ኮድ 0065 የብር 1,049,512.62 ብቻ የተያዘ በመሆኑ ልዩነቱ የብር 47,425.34 የተከፋይ ሂሳብ ዝቅ እንዲል ያደረገው መሆኑ።

3. የዩኒርስቲው ሆስፒታል በቀን 25/06/201 በpv 382313 ከመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የብር 378,532.63 ና በቀን 17/09/2013 በpv82640 ብር764,644.17 በድምሩ የብር 1,143,176.80 የመድሀኒት ግዢ ሲፈጽም የሽያጭ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባው ሳይቀርብ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ክፍያ ተፈፅሞና ሂሳቡ ተወራርዶ ተገኝቷል ፡፡
4. ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ
   - ✓ ከመደበኛ በጀት ብር 44,211,638.74
   - ✓ ከካፒታል በጀት ብር 3,439,602.34 በድምሩ ብር 47,651,241.08 መኖሩ

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

<u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤</u>

1. ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሪፖርት የተላከዉ የተቋራጮች መያዣ ሂሳብ /ሪቴንሽን 5061/ ውስጥ የ48 ተቋራጮች ድምር የብር5,603,624.95 በግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዝርዝራቸው ቢኖርም በIBEX በተቋራጮች ስም ተቀጸላ ሌጀር ኮድ ያልተከፈለታቸው መሆኑ
2. በሪፈራል ሆስፒታል በሻምቡ የፋርማሲ ቤት ክራይ ግዥ በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም ሲገባ በቀጥታ ግዢ ብር 240,000.00 ክፍያ በመፈፀሙ መንግስት ከውድድር ሊያገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አሳጥቶታል፡፡
3. በዩኒቨርሲቲ /ዋና ግቢ/ አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ለዎርክ ሾፕ ስራ የሚዉሉ ዕቃዎችና ለጥበቃና ደህንነት ሰራተኞች የደንብ ልብስ ግዥ በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም ሲገባ በዋጋ ማወዳደሪያ ተከፋፍሎ

በድምሩ ብር 1,360,526.47 ማቅረቢያ ግዥ የተገዙ በመሆኑ መንግስት ከውድድር ሊያገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አሳጥቶታል፡፡

4. ዩኒቨርሲቲዉ በድምሩ የብር 252,756.00 ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውል የህክምና መድሃኒቶች፣ ግዥ ሲፈጸም ከመድኃኒት ፈንድ እና የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ አቅርቦቶቹ መዲሀንቶቹ አለመኖራቸዉን (Stock out) ማስረጃ ሳይቀርብ ከሌሎች የግል መድኃኒት አቅራቢዎች ግዥ የፈጸመ መሆኑ፣
5. በጠቅላላ ድምሩ የብር 909,632.06 ቀጣይነት እና ዘላቂነት ባላቸው የስራ ዘርፎች ቋሚ የስራ መደብ እንዲሆኑ ጥናት በማድረግ መዋቅር ለሚኒስቴሩ በማስፈቀድ ክፍያውን መፈጸም ሲገባ በቀን ሰራተኝነት ብር 150.00፣ 50.00 እና 40.00 የክፍያ ተመን በማድረግ መመሪያን ባልተከተለ መልኩ ለቀን ሰራተኞቹ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ
6. ሳይወራረድ ከ 1ዓመት እስከ 10 ዓመት ያስቆጠረ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 340,389.83 መኖሩ፣
7. ሳይወራረድ ከ 1ዓመት እስከ 5 ዓመት ያስቆጠረ የተከፋይ ሂሳብ ብር 684,268.00 መኖሩ፣
8. ስራ ላይ ያልዋለ በጀት
   - ✓ ከመደበኛ በጀት ብር 54,550,589.07
   - ✓ ከካፒታል በጀት ብር 59,762,941.65 እና
   - ✓ ከውስጥ ገቢ ብር 19,507,222.29 በድምሩ ብር 133,820,753.01 መኖሩ

የ2011 በጀት ዓመት እርምጃ ያልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች

- በ2011 በጀት ዓመት የተከታታይ ትምህርት መርሃ ግብር ፕሮግራም ላስተማሩ እንግዳ መምህራን ክፍያ ሲፈጸም መምህራኑ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ብቻ ያቀረቡ በመሆኑ ከክፍያው ላይ 30% ቅድመ ግብር ተቀናሽ መደረግ ሲገባው 2% ብቻ በመቀነሱ ብር 22,176.00 የግብር ሂሳብ ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

ሌሎች ጉዳዮች፤

ምንም እንኳን በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖራቸውም መሠረታዊና ጉልህ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥርና የአፈጻጸም ድክመቶች ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የንብረት አመዘጋገብ፤ አያያዝ እና አጠባበቅ በፌደራል መንግስት ግዢና ንብረት አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 649/2001 መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

የማዕከል በአላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት

- በአላቂ ንብረት ግምጃ ቤቱ እስቶክ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ፤ የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ና የማመዛዘን ስራ በአንድ ባለሙያ የሚከናወን መሆኑ

የማዕከል በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት

- የቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት የንብረት ገቢ (ሞዴል 19) ፤ የንብረት ወጪ (ሞዴል 22) ስራ በአንድ የግምጃ ቤቱ ባለሙያ የሚከናወን መሆኑ
- በግምጃ ቤቱ ውስጥ አገልግሎት አይሰጡም ተብሎ ተቀመጡ በርካታ ንብረቶች እንደነ ኮምፒተር ብዛታቸዉ 357፤የመኪና መለዋወጫ፣ አሮጌ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች ብዛታቸዉ 433 የሚሆን የመኪና ጎማዎች፣ 35 ኩንታል የምስር ክክ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ

ተሽከርካሪን በተመለከተ

- ልብሬ እና ታልጋ የሌለዉ ባለበትነቱ የማይታወቅ አራት ትራክተር ለአመታት የቆዩ መሆኑ ፡፡
- በግምጃ ቤቱ እስቶክ የሚያመዛዝን ባለሙያ እና የመለዋዎጫ ዕቃዎችን በዳታ መዝግቦ የሚይዝ /ዳታ ኢንኮደር/ ባለሙያ ያልተሟላ መሆኑ ፤

በሪፈራል ሆስፒታል የአላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት

- በአላቂ ንብረት ግምጃ ቤቱ እስቶክ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ፤ የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ና የማመዛዘን ስራ በአንድ ባለሙያ የሚከናወን መሆኑ
- በአላቂ ንብርት ክፍል ውስጥ ቢን ካርድ እና እስቶክ ካርድ ስርዓት የማይተገበር መሆኑ፡፡

የሪፈራል ሆስፒታል የቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤትን በተመለከት

- የቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት የንብረት ገቢ (ሞዴል 19) ፤ የንብረት ወጪ (ሞዴል 22) ስራ በአንድ የግምጃ ቤቱ ባለሙያ የሚከናወን መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ ውስጥ የህክምና መሳሪያ እንደነ x-ray ማሽን እና dental x-ray ማሽን ከአንድ ዓመት በላይ ሜዳ ላይ ተጥሎ የተቀመጡ መሆኑን እንዲሁም በሆስፒታሉ ገቢ ዉስጥ የቋሚ እስቶር የሌሌ በመሆኑ እቃዎቹ ሜዳ ላይ የተከማቹ የሚገኙ መሆኑ፡፡

ወርቅአፈራሁ ወንድምአገኘሁ
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

መጋቢት 2014

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የወለጋ ዩኒቨርሲቲ

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የወለጋ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፤

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡ የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የወለጋ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

1.1. <u>አቅራቢዎች በውላቸው መሰረት ባለማቅረባቸው ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ</u>

1.1.1. <u>ግኝት</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) መሠረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቅቆ ባያስረክብ፣ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4/ሀ መሰረት ደግሞ ከፍ ሲል በመመሪያው አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) መሠረት አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ለዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው እና በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን 10% መብለጥ እንዳሌለበት በግልፅ ተቀምጧል፡፡ መመሪያዉን መሰረት በማድረግ የዩኒቨርሲቲዉ የዉል አስተዳደር ኦዲት ሲደረግ፡-

ዩኒቨርሲቲዉ በዉላቸዉ በተጠቀሰዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ዉላቸዉን ያላጠናቀቁ አቅራቢዎች ዩኒቨርሲቲዉን ላስተጓጎሉበት ከሁለት አቅራቢዎች በድምሩ የብር 205,631.1 የጉዳት ካሳ ከአቅራቢዎች ሰብስቦ/ቀንሶ/ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ማድረግ ሲገባ ያላደረገ መሆኑን በኦዲት ታይቷል። *(ዝርዝሩን በአባሪ 1 ተመልክቷል፡፡)*

1.1.2. <u>ሥጋት</u>

አቅራቢዎች በውለታው መሰረት ባለመፈጸማቸው መከፈል ያለበት የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ክፍያ መፈጸም መንግስት /ተቋሙ/ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡ እንዲሁም አቅራቢዎቹ በዉላቸዉ ላይ በተጠቀሰዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ አቅርቦታቸዉን ካላቀረቡና ባላቀረቡባቸዉ በመመሪያዉ መሰረት ተገቢዉን የገንዘብ ቅጣት /የጉዳት ካሳ/ ካልተቀጡ አጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዉን የዉል አስተዳደር ተዓማኒነት ሊያሳጣዉ ይችላል፡፡

1.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

መከፈል የሚገባው የጉዳት ካሳ ከሚመለከተው አካል ተሰብስቦ ዩኒቨርሲቲዉ ገቢ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል። ለወደፊቱም አቅራቢዎች በውላቸው መሠረት ማጠናቀቃቸውን ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

1.1.4. <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ምላሽ አልተሰጠበትም

1.2. <u>በማነስ የተመዘገበ የሪቴንሽን ሂሳብ /5061/</u>

1.2.1. <u>ግኝት</u>

- ዩኒቨርሲቲዉ ለስፍለን ኢንጂነሪንግ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በዋናዉ ግቢ የሌክቸር ሆል /lecture whole/ እድሳት ስራ አከናዉኖ የመጨረሻ የሪቴንሽን/2.5%/ በቀን 10/05/2013 በPV ቁጥር 268498 የብር 366,363.47 ተመላሽ ክፍያ ቢፈጽምም ነገር ግን በተቋራጩ ተቀጽላ ሌጀር ኮድ 5061 0057 ብር 28,869.40 በክሬዲት የተያዘዉ በመሆኑ አለአግባብ የተከፋይ ሂሳብ ከፍ ያለ መሆኑ
- ለኤልናፍ ኢንጂነሪንግ በግንቢ ካምፓስ የኢንፍራስትራክቸር ቀሪ ግንባታ ስራ ላከናወነበት በ9ኛ ዙር የክፍያ የምስክር ወረቀት በቀን 24/09/2013 በPV ቁጥር 89018 የብር 2,836,292.44 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን በቀረበዉ የክፍያ ምስክር ወረቀት መሰረት የሪቴንሽን 5061 የብር 1,096,937.96 የተያዘ ሲሆን በተቋራጩ የተቀጽላ ሌጀር ኮድ 0065 የብር 1,049,512.62 ብቻ የተያዘ ቢሆንም ነገር ግን ለክፍያ የቀረበዉ የ9ኛ ክፍያ ምስክር ወረቀት ላይ ላይ እስከ 9ኛ ክፍያ ተቋራጩ ስለሪቴንሽን ያስያዘዉ ብር 1,096,937.96 /21,938,759.12* 5% የሚያሳይ በመሆኑ ልዩነቱ የብር 47,425.34 የተከፋይ ሂሳብ ዝቅ እንዲል ያደረገው መሆኑ።

1.2.2. <u>ስጋት</u>

- የሪቴንሽን ሂሳብ አመዘጋገብ፣ አያያዝና አስተዳደር ግልጽነት ላይኖረዉ ይችላል።
- የማይከፈል ወይም ተመላሽ የማይደረግ የሪቴንሽን ሂሳብ የሂሳብ ሪፖርቱን ሚዛን ሊያዛባዉ ይችላል።

1.2.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

አስፈላጊዉ ማስተካከያ ተሰርቶ ለኦዲት መቅርብ ይኖርበታል።

1.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የተቀመጠዉ ግኝትን አስመልክቶ ምዝገባዉ በስህተት በሌላ ተቀጽላ ሌጀር ላይ ተመዝግቦ ከሆነ የሚጣራ ሲሆን የመጨረሻው ክፍያ ሲከፈል የሚስተካከል ይሆናል፡፡

1.3. የዋስትና ሂሳብ /ሪቴንሽን/ ተቀጽላ ሌጀር አለመኖር

1.3.1. ግኝት

- ሰኔ 30/2013 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላከዉ የተቋራጮች መያዣ ሂሳብ /ሪቴንሽን 5061/ ከጠቅላላዉ የ143 ተቋራጮች በድምሩ የብር 64,871,014.78 የ48 ተቋራጮች የብር5,603,624.95 በተቋራጮች ስም ተቀጽላ ሌጀር ኮድ ከግንባታ ጽህፈት ቤት የተገኘ ሲሆን ለእንዳንዳቸው በአይቤክስ ኮድ ያልተከፈለታቸው መሆኑ፡፡ /ዝርዝሩ 2 በአባሪ ተመልክቷል፡፡/

1.3.2. ሥጋት

- በየተቋራጮቹ ስም የተከፋይ ተቀጽላ ሌጀር ኮድ ከሌለ የእያንዳንዱን ተቋራጭ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ማጣራት ስለሚያዳግት ሚዛኑን ታዓማኒነት ሊያሳጣዉ ይችላል፡፡ እንዲሁም የሚወራረድና የማይወራረደዉን ለይቶ ለማዉጣት ሊያዳግት ይችላል፡፡

1.3.3. የማሻሻያ ሀሳብ

ለያንዳንዱ ተቋራጭ ተቀጽላ ሌጀር ኮድ በመክፈት በድምሩ የታየዉን የ5061 ሂሳብ እያንዳንዱ ተቋራጭ ሂሳብ ሚዛን ለይቶ ሪፖርቱ እንዲሰተካከል ማድረግ ይኖርባቸዋል።

1.3.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

በዋስትና መያዣ (ሪቴንሽን) 5061 አስመልክቶ ለቀረበው ግኝት ለተወሰኑ ድርጅቶች የተቀጽላ ሌጀር ያልተሰጣቸው መሆኑን በመግለጽ በግኝቱ ላይ የታየው እንደሚታወቀው ዩኒቨርሲቲያችን እንደ አዲስ ሲጀመር በሁሉም ተከፋይ እና ተሰብሳቢ ሂሳብ መደቦች ላይ እንደ አጠቃላይ ሲሰራ የቆየ በመሆኑ ተቀጽላ ሌጀር ለድርጅቶች መስጠት የተጀመረው ቅርብ ጊዜ በመሆኑ ለወደፊቱ ለቀረበው ግኝት አይተን አስፈላጊውን ማስተካከያ የሚናደርግ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

1.4. በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ክፍያ የተፈፀመና የተወራረደ ክፍያን በተመለከተ/ሪፈራል ሆስፒታል/

1.4.1. ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች ንዑስ ቁጥር

7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋናው ደረሰኝ መሆን እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ ነገር ግን ሆስፒታሉ በቀን 25/06/201 በpv 382313 ለመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የብር 378,532.63 ና በቀን 17/09/2013 በpv82640 የብር764,644.17 በድምሩ የብር 1,143,176.80 የአገልግሎት/ዕቃ ግዥ ክፍያ ሲፈጽም ተገቢ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መቀበል ሲገባዉ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ ተገኝቷል ፡፡ ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ነው፡-

1.4.2. <u>ሥጋት፣</u>

በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ሂሳብ ማወራረድና መመዝገብ ሂሳቡ በድጋሚ ክፍያ ሊጠየቅበት የሚችልበትን ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡ በተጨማሪም ከድርጅቶቹ ለሚፈለግ የመንግስት ግብርና ታክስ ለክትትልና ቁጥጥር አመቺ ላይሆን ይችላል፡፡

1.4.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ሂሳብ የተወራረድ ደረሰኝ ሊቀርብለት ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ለወጪ ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ ሳይረጋገጥ ሂሳቡ እንዳይወራረድ እና እንዳይመዘገብ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

1.4.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ለወሊጋ ዩኒቨርሲቲ ቲቼንግና ሪፈራል ሆስፒታል ከመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የተለያዩ መድሃኒቶች ተገዝተው ስራ ላይ የዋሉ ሲሆን በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ሂሳቡ የተወራረደ ቢሆንም ግገርው ከመንግስት መስሪያ ቤት የተገዛ በመሆኑ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ማያያዝ አስፈላጊ ቢሆንም በስህተት ያልተያያዘ ስለሆነ ለወደፊቱ እንዲህ አይነት ስህተቶች እንዳይፈጠሩ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ የምንወስድ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

1.4.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ግገርው ከመንግስት መስሪያ ቤትም ሆነ ከግል ቢገዛም የቀረበው የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ከሆነ መመዝገብ ያለበት በተከፋይ ሲሆን ክፍያው ተፈጽሞ ጥሬ ገንዘብ ክሬዲት ከተመዘገበ የግድ ደረሰኝ ሊቀርብለት ይገባል፡፡

1.5.የገቢያ ጥናትን ያላካተተና የከፋፍሎ /ፕሮፎርማ/ ግዥ

1.5.1 ግኝት

ሰኔ2002 ዓ.ም የወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 24/1፣ እና አንቀጽ 24.3 ፊደል ሀ እና ለ፣ አንቀጽ 24.12 እንደ ቅደም ተከተላቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸውና ሆኖም ሊታቀዱ ያልቻሉ እና ዋጋቸው ታህሳስ 12/2008 ዓ.ም ተግባራዊ እንዲደረግ በተደረገው የተሻሻለው መመሪያ ለዕቃ ብር 200,000.00 ለአገልግሎት ግዥ ብር 150,000.00 በእነዚህ ገደብ ውስጥ የሚገመቱ ግዢዎች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ዘዴ መፈጸም እንደሚቻል፤እንዲሁም የመንግስት መ/ቤቱ የዋጋ ማቅረቢያ በመስጠት እና ዋጋ በመወሰን ሂደት ሊፈጠር የሚችል መመሳጠርን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር በመከተል እና መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር፣ በግዥ ስራ ክፍሉ የሚካሄድ የገቢያ ጥናትን በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማመን እና በየጊዜው ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ እና የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት እንደሌለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የተገዙትን እቃዎች ኦዲት ሲደረግ፦

- በዩኒቨርሲቲ /ዋና ግቢ/ አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ለዎርክ ሾፕ ስራ የሚዉሉ ዕቃዎችና ለጥበቃና ደህንነት ሰራተኞች የደንብ ልብስ ግዥ በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም ሲገባ በዋጋ ማወዳደሪያ ተከፋፍሎ በድምሩ ብር 1,360,526.47 ማቅረቢያ ግዥ የተገዙ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡ */ዝርዝሩ አባሪ 3 ተመልክቷል፡፡/*

1.5.2 ሥጋት

- በመንግሥት ታምነው የሚወጡ መመሪያዎችን መጣስ ተጠያቂነትን ሊያመጣ ይችላል፡፡
- በግዥ ሥራ ክፍሉ የተደረገው የገቢያ ጥናት ዋጋ እና በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ትክክለኛው የገበያ ዋጋ ሳይታወቅ የሚፈጸም ግዥ ዋጋው የተጋነነ እና መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርገው ይችላል፡፡

- ግዥ በአዋጅና መመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባ፣ የአፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፤

1.5.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

- ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ዩኒቨርሲቲው በጥቅል ወይም በጅምላ ሲገዙ የሚችሉ ዕቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም አለበት፡፡
- ዩኒቨርስቲው ዋና ግቢ በአብዛኛው ለዎርክ ሾፕ የተገዛ እቃዎች ግልፅ ጨረታ አዉጥቶ መግዛት ሲኖርበት፤ በዋጋ ማወዳደሪያ ያለገቢያ ጥናት የተገዛበት ሁኔታ አግባብ ባለመሆኑ አሰራሩ በአስቸኳይ እንዲቆም እንዲደረግ፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በዋጋ ማወዳደሪያ የሚገዙ የእቃ ግዥ ላይ የተቋሙ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

1.5.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

እንደሚታወቀው ዩኒቨርሲቲያችን መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት እንደ ሀገር በተከሰተው የኮቪድ 19 በሽታን አስመልክቶ የማቆያ ማዕከል ሆኖ እንዲያገለግል በተወሰነው መሰረት ለዚህ አገልግሎት የሚውል ብዙ ዶርሚተሪዎች እድሳት የተደረገ በመሆኑ አንዳንድ እቃዎች በግልጽ ጨረታ ያልተካተቱ እና በአስቸኳይ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በኢንጂነሪንግ ዎርክሾፕ በኩል ዕቃዎች ተገዝቶ ስራ የተከናወነ ሲሆን ለወደፊቱ መመሪያው በሚያስቀምጠው መሰረት የምንፈጽም ይሆናል፡፡

ከላይ የተለያዩ ግዥዎች እንደተፈጸሙና ግዥዎቹ በተቀመጠዉ የግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት አለመሆን የተገለጸ ሲሆን የተገዛዉ ዕቃ ለመማር ማስተማሪ አገልግሎት ሳይታቀዱ በCovid-19 ምክንያት ተማሪዎች ተራርቀዉ እንዲቀመጡና ለመስራት ግዴታ የሆኑትን የመማሪያ ክፍል ወርክሾፕ አለሙኒየም ፓረቲሽን መስራትና የወርክ ሾፕ ቤንች መስራት የፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት ቢሮ በነበረበት ቢሮ ጥበትና እንግዶችን ለማስተናገድ ምቹ ካለመሆን የተነሳ በአዲስ መልክ የተስተካከለና Covid-19 ምክንያት ሰዎችን ርቀት ለመጠበቅ አሉሚኒየም ፓርቲሽንና ቤት ጥገና በአስቸኳይ ኢንዲሰራ ስለተፈለገ ፕሮፎርማ ግዥ የተገዙና የተሰሩ ሲሆን ለወደፊቱ ግን በግልጽ ጨረታ ታቅደዉ እንዲገዙ እናደርጋለን፡፡

1.6 በቀጥታ ግዥ

1.6.1 ግኝት

ሰኔ/2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.2-15.4 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያትና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል። ግዥዎች በመመሪያው መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ -

- በሪፌራል ሆስፒታሉ ከመመሪያው ውጭ ያለውድድር በቀጥታ ግዥ በሻምቡ የፋርማሲ ቤት ኪራይ በቀጥታ ግዥ ተፈፅሞ ብር 240,000.00 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

1.6.2 ሥጋት፣

- ግዥ በመመሪያ መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥት ገንዘብም ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

1.6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ካምፓሱ ማናቸውንም ግዥ ሆነ ክፍያ ሲፈጽም አዋጆችን ፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን መሰረት ያደረገ አሰራር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት በቀጥታ ግዥ ሊፈፀም የቻለበት ተገቢው ማብራሪያ መቅረብ እንዳለበት ሆኖ ወደፊት መሰል ችግሮች እንዳይፈፀም ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል ፡፡

1.6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ምላሽ አልተሰጠበትም፡፡

1.7 ከሌሎች የግል መድኃኒት አቅራቢዎች የተፈጸመ የመድሐኒት ግዥ

1.7.1 ግኝት፣

የመድኃኒት ፈንድ እና የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ ለማቋቋም በወጣ አዋጅ 553/1999 አንቀጽ 15/2 መንግስታዊ የጤና ተቋማት በሙሉ የመሰረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት ፍላጎታቸውን በቀጥታ ለኤጀንሲው ብቻ ጥያቄ በማቅረብ ይገለገላሉ ይላል፡፡ ኤጀንሲው የተጠቀሱትን መድኃኒቶች ለማቅረብ በማይችልበት ወቅት ለጠያቂዎች ተገቢውን አማራጭ መፍትሔ እንደሚሰጥ ይደነግጋል፡፡ መመሪያዉን መሰረት በማድረግ የዩኒቨርሲቲዉ የመዲሀኒት ግዥ ሂደት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- ❖ ዩኒቨርሲቲዉ በቀን 10/06/2013 ዓ/ም በወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 748151 ብር 184,332.00 ናበቀን 23/04/2013 ዓ/ም በወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 743749 የብር 68,424.00 በድምሩ የብር 252,756.00 ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውል የህክምና መድሃኒቶች፣ ግዥ ሲፈጸም ከመድኃኒት ፈንድ እና የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ አቅርቦቶቹ መዲሀንቶቹ አለመኖራቸዉን (Stock out) ማስረጃ ሳይቀርብ ከሌሎች የግል መድኃኒት አቅራቢዎች ግዥ የፈጸመ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

1.7.2 ሥጋት፣

- ❖ በመንግስት ታምነው የሚወጡ መመሪያዎችን መጣስ ተጠያቂነት ሊያመጣ ይችላል፡፡
- ❖ አቅርቦቱ ከኤጀንሲው የሌለ መሆኑን ሳይታወቅ ከሌሎች የግል አቅራቢዎች መግዛቱ በተመጣጣኝ ዋጋና ጥራት ላይገዙ ስለሚችሉ መንግስት ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

1.7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ❖ መድሃኒቶች፣ መሳሪያዎችና የላብራቶሪ ሪኤጀንቶች ግዥ ሲፈጸም ለመድኃኒት ፈንድ እና የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ አቅርቦቶቹ እንደሌሉ (Stock out) እንደሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
- ❖ ከሪፈራል ሆስፒታል መሰረታዊ የመድኃኒት አቅርቦት ፍላጎታቸውን በቀጥታ ለኤጀንሲው ብቻ ጥያቄ በማቅረብ መገልገል እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ሆኖም ግን ኤጀንሲው የተጠቀሱትን የመድኃኒት ለማቅረብ በማይችልበት ወቅት ለጠያቂዎች ተገቢውን አማራጭ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም ግዥ ሲፈጸም ኤጀንሲው አቅርቦቱን ማቅረብ እንደሚችል እና እንደማይችል ተጠይቆ በሚሰጠው ምላሽና

ማስረጃ መሰረት ተገቢውን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይኖር ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊኖርይገባል

1.7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ከመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ (Stock out) ሳይኖር የመድሃኒት ግዢ ተፈፅሟል ለተባለው እንደሀገር በተከሰተው Covid-19 ምክንያት በጣም አስቸኳይ የሚፈለጉ መድሃኒቶች ከግል ድርጅቶች በፕሮፎርማ የተገዙ ሲሆን ሌላው ግን በህጉ መሰረት እየተሰራ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

1.8 ዘላቂነት ባላቸው የስራ መደቦች ላይ የተከፈለ የቀን ሰራተኞች ክፍያ

1.8.1 ግኝት

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር መ80-839/1 በተፃፈ ደብዳቤ ዘላቂነት ባለውና በተመደበ የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) በፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች ተቀጥረው ያልተቋረጠ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ሠራተኞች በቋሚነት እንዲመደቡ፣ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባልተመደበና ዘላቂነት በሌለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ መሰናበት እንዳለባቸው፣ ይህ መመሪያ ለአንድ ጊዜ አፈፃፀም ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል እንዲሁም እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በመጀመሪያ ለሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት መመሪያ መተላለፉ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርስቲዉ የሠራተኛ እጥረት በማለት ለተለያየ ስራ ለሚሰሩ የቀን ሰራተኞች በጠቅላላ ድምሩ የብር 909,632.06 ቀጣይነት እና ዘላቂነት ባላቸው የስራ ዘርፎች ቋሚ የስራ መደብ እንዲሆኑ ጥናት በማድረግ መዋቅር ለሚኒስቴሩ በማስፈቀድ ክፍያውን መፈጸም ሲገባ በቀን ሰራተኝነት ብር 150.00፣ 50.00 እና 40.00 የክፍያ ተመን በማድረግ መመሪያን ባልተከተለ መልኩ ለቀን ሰራተኞቹ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡

1.8.2 ሥጋት፣

አሰራሩ በመንግስት የበጀት አጠቃቀምና በእቅድ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ችግር ከማስከተሉም በተጨማሪ ዘላቂነት ባላቸው የስራ መደቦች ሰራተኞችን በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት የሰው ሃይል በዕቅድ እንዳይመራና በመንግስት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ሊያስከትል ይችላል፡፡

1.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በተመደበ የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ የስራ መደቦቹ በቋሚ ሰራተኞች በውስጥ ደረጃ እድገት ወይም በውጭ ቅጥር ማስታወቂያ በማውጣት ሰራተኞቹ ሊመደቡ /ሊቀጠሩ/ይገባል፡፡ በቀን ሰራተኛነት እየተከፈለ ያለው ክፍያም ሊቆም ይገባል፡፡ ለወደፊቱ እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በማሳወቅ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.8.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በዩኒቨርሲቲያችን ስር የሚገኙ ቀን ሰራተኞች ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመ ጀምሮ ከዩኒቨርሲቲው ጋር በተማሪዎች ምግብ ቤት አካባቢ በቀን ሰራተኝነት ሲሰሩ የቆዩና በመስራት ላይ የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህ የቀን ሰራተኞች ዩኒቨርሲቲው ባለው መዋቅር ላይ ማስታወቂያ አውጥቶ ብዙ የቀን ሰራተኞች ቋሚነትን ያገኙ ሲሆን ለወደፊቱም መንግስት በሚፈቅድልን መዋቅር መሰረት በተመደበልን የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በህጉ መሰረት አወዳድረን ወደ ቋሚነት የምናስገባ መሆናችንን እንገልፃለን፡፡

2 የተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 በወቅቱ ያልተወራረዱ የተሰብሳቢ ሂሳቦች

2.1.1 ግኝት

በፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ ቁጥር 4 ተሰብሳቢ ሂሳብ (መ) ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልፃል።

ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የተሰብሳቢ ሂሳብ መደቦች ከተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የሚሰበሰብ የመንግስት ገንዘብ በተሰብሳቢነት የሚታዩ ሂሳቦች መወራረድ ባለባቸው ወቅት እንደማይወራረዱና እየተንከባለሉ የሚሄዱ መሆኑንና በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 340,389.83 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ያለ ሲሆን ይህም፣

የሂሳብ መደብ		ተሰብሳቢ ሂሳቡ የቆይታ ጊዜ				
		ከ1 ወር-1 ዓመት	ከ1-5 ዓመት	ከ5-10ዓመት	ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የተወራረደ	
4202				156,556.83	0.00	156,556.83
4211			33,833.00		0.00	33,833.00
4274			378,890.00		228,890.00	150,000.00
ድምር			412,723.00	156,556.83	228,890.00	340,389.83

2.1.2 ስጋት፣

ሂሳቡ በወቅቱ ካልተወራረደ የመንግስት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ባክኖ ሊቀር የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ በተጨማሪም በሂሳብ መግለጫው ላይ በየዓመቱ በተደጋጋሚ እንዲታይ ከማድረጉም ሌላ የዩኒቨርሲቲው በጀት አላግባብ እንዲቀነስ ያደርገዋል፡፡

2.1.3 ማሻሻያ ሀሳብ፣

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ እና መሰብሰብ የሚገባቸው ከሚመለከታቸው አካላት ተሰብሲቦ ገቢ እንዲደረጉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- በ2013 በጀት ዓመት የዩኒቨርሲቲው ፋይናንሻል ሪፖርት ላይ የሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ አስመልክቶ በግኝት የታየው በሂሳብ መደብ 4202 ላይ የገንዘብ ያገሮች ጉድለት ከታየበት ጀምሮ በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያለ መሆኑን እና ለወደፊቱ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን አስፈላጊውን እርምጃ የሚወሰድ መሆኑ፣

➢ በሂሳብ መደብ 4211 ላይ የሚታየው ገንዘብ በዩኒቨርሲቲው ዕቃ ግዥ ሰራተኛ በሆኑ አቶ ጸጋዬ ጨመዳ እጅ የሚገኝ ብር 33,833.00 ሲሆን ለምህንድስና እና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ኬብል ግዥ ወጪ የተደረገና ዕቃው ገቢ ተደርጎ ያልቀረበ በመሆኑ ሰራተኛው

አስፈላጊውን ሰነድ አቅርቦ ሂሳቡን እንዲያወራርድ ወይም ገንዘቡን ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲያደርግ ደብዳቤ የተጻፈበት መሆኑ፣

➢ በሂሳብ መደብ 4274 ላይ የሚታየው ገንዘብ 150,000.00 ከዌብኮን ኮንስትራክሽን የሚፈለግ በመሆኑ ድርጅቱ ለሰራው ስራ ክፍያ ያልተፈፀመለት በመሆኑ ከሚያቀርው የክፍያ ሰርቲፍኬት ላይ ተቀናሽ የሚደረግ ይሆናል፡፡

3 ተከፋይ ሂሳብ

3.1 በወቅቱ ያልተሰበሰቡ የተከፋይ ሂሳቦች

3.1.1 ግኝት፣

የዩኒቨርስቲው ተከፋይ ሂሳብ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በድምሩ ብር 684,268.00 ያለ ሲሆን ከአንድ እስከ ሶስት ዓመት በላይ እየተንከባለለ የመጣና እስከ ሰኔ 30/2013 ድረስ ያልተወራረዱ መሆኑ ታይቷል፡፡

የሂሳብ መደብ		የተከፋይ ሂሳቡ የቆይታ ጊዜ			
		ከአንድ ወር - አንድ ዓመት	ከአንድ ዓመት - አምስት ዓመት	ከአምስት - አስር ዓመት	ከአስር ዓመት በላይ
5028			63,328.00		
5054			620,940.00		
ድምር			684,268.00		

3.1.2 ሥጋት፣

የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ካልተወራረደ ወይም ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተአማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

3.1.3 ማሻሻያ ሀሳብ፣

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል መከፈል ይኖርባቸዋ፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ግን የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

3.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- በ2013 በጀት ዓመት በዩኒቨርሲቲው ፋይናንሻል ሪፖርት ላይ የታየው ተከፋይ ሂሳብ በሂሳብ መደብ 5028 ላይ ብር 63,328.00 የሚታየው ሲሆን ለሆቴሎችና እንስሳት

እርባታ ማዕከል ለእንስሳት አገልግሎት የሚውል የተላከ በመሆኑ በ2013 በጀት ዓመት በአከባቢው በተከሰተው አለመረጋጋት ምክኒያት ተያይዞ ክፍያው የቀረበ ጥያቄ ባለመኖሩ ሊታይ ችሏል፡፡ ሆኖም ግን በ2014 በጀት ዓመት የክፍያ ጥያቄ የማይቀርብ ከሆነ ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ተመላሽ የሚደረግ መሆኑን እና በሂሳብ መደብ 5054 ላይ የሚታየው ብር **620,940.00** ለጤና ኮሌጅ ተማሪዎች አገልግሎት የሚውል በኦሮሚያ ጤና ቢሮ ተልኮ በ2014 በጀት ዓመት በሚያቀርቡት የክፍያ ጥያቄ መሰረት የሚከፈል ይሆናል፡፡

4 <u>በጀት አጠቃቀም</u>

4.1 <u>ግኝት፣</u>

በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ በዚህዉ መሰረት የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከተው ተገኝቷል፡፡

- ከመደበኛ በጀት ብር **54,550,589.07**፣ ከካፒታል በጀት ብር **59,762,941.65**፣ ከውስጥ ገቢ ወጪ ብር **19,507,222.29** በድምሩ ብር **133,820,753.01** ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣ እንዲሁም
- ከመደበኛ በጀት ብር 44,211,638.74 ከካፒታል በጀት ብር **3,439,602.34** በድምሩ የብር 47,651,241.08 ከተፈቀደለት የሂሳብ መደብ ጣሪያ በላይ የተጠቀሙበት መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡ */ ዝርዝሩ በአባሪ 5 ቀርቧል/*

4.2 <u>ሥጋት፣</u>

- የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም መመሪያን ከመጣሱም ባሻገር የመንግሥትን ውስን ሀብት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- የወጪ በጀቱ በእቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱ ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በጀት ሳይፈቀድ፣ተጨማሪ በጀት ሳይጠየቅ ወይም ዝውውር ሳይደረግ ወጪ መፈጸም አግባብ ባለመሆኑ አሰራሩ እንዲስተካከል እና የዩኒቨርሲቲው ዕቅድና ክንውን የተጣጣመ እንዲሆን መደረግ ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በ2013 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀምን አስመልክቶ በግኝት ላይ የተቀመጠው ከበጀት በላይ እና ከበጀት በታች ወይም በስራ ላይ ያልዋለው በጀት ከመደበኛ ስራ ላይ ሳይውል ቀርቷል ለተባለው በአንዳንድ የሂሳብ መደቦች ላይ ለምሳሌ የተማሪ ቀለብ የተፈቀደው በጀት በቂ ባለመሆኑ ከተፈቀደው ጣሪያ በላይ የተጠቀምን ሲሆን የሌላውን የበጀት ሂሳብ ኮድ የሚነካ በመሆኑ እንዲሁም በሁሉም ፕሮግራም ላይ ተጨማሪ በጀት ጠይቀን እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ሳይፈቀድ ቆይቶ የተፈቀደልን በመሆኑ በአንዳንድ ሂሳብ ሳንጠቀም ቀርተናል፡፡

- ከካፒታል በጀት ስራ ላይ ሳይውል የቀረው በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ተይዞ 4251 የተከፈለ በመሆኑ የበጀት ሂሳብ ኮድን ያልነካ ሲሆን በበጀት እንጂ በብር ደረጃ ቀሪ በጀት የሌለ በመሆኑ እና እንዲሁም የውስጥ ገቢ አስመልክቶ ስራ ላይ ሳይውል የቀረው የተሰበሰበው ገቢ በቂ ባለመሆኑ የተፈቀደውን በጀት ሙሉ በሙሉ ሳንጠቀም ቀርተናል፡፡
- በአንዳንድ የሂሳብ መደቦች ላይ ከተፈቀደው ጣሪያ በላይ የተጠቀምንበት ምክኒያት ዋናው የተማሪ ቀለብ በ6216 ላይ የታየው ሲሆን በሌሎች የሂሳብ መደቦች ከጣሪያ በላይ የተጠቀምንበት ምክኒያት በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በ2012 በጀት ዓመት የሚሰሩ ስራዎች ሳይሰሩ ቀርተው ወደ 2013 በጀት ዓመት ተከምሮ በመምጣቱ ለምሳሌ በ2012 በጀት ዓመት የሚመረቁ ተማሪዎች ወደ 2013 በጀት ዓመት ተሸጋግሮ ምርቃቱ የተከናወነ ሲሆን በተጨማሪም ለተማሪዎች የተግባር ትምህርት የተከፈለ በመሆኑ ከተፈቀደው ጣሪያ በላይ ልንጠቀም ችለናል፡፡
- እንዲሁም በካፒታል በጀት ከጣሪያ በላይ አጠቃቀሙ የታየው የውጭ መምህራን ደመወዝ የዶላር ምንዛሪ በመጨመሩ ምክኒያት እና በሌሎች አንዳንድ የሂሳብ መደቦች ላይ ተጨማሪ በጀት ጠይቀን ወደ ዓመቱ መጨረሻ የተፈቀደ በመሆኑ የበጀት ዝውውር መስራት ባለመቻላችን ሊታይ ችሏል፡፡

5 የንብረት አስተዳደር፣

5.1 የዩኒቨርሲቲዉ የንብረት አጠቃቀምና አስተዳደር

5.1.1 ግኝት፤

በፌዴራል መንግስት አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ ፣ የመጠቀም ፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንደሚገባ በአዋጁና በመመሪያው ተቀምጧል፡፡ በዚህዉ መሰረት የወሊጋ ዩኒቨርሲቲ በመንግስት አዋጅና መመሪያ መሰረት የንብረት አያያዝ ፣ አጠቃቀም እና አመዘጋገብ ለማየት ኦዲት ሲደረግ:

የማዕከል በአላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት

- በአላቂ ንብረት ግምጃ ቤቱ እስቶክ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ፤ የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ና የማመዛዘን ስራ በአንድ ባለሙያ የሚከናወን መሆኑ

የማዕከል በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት

- የቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት የንብረት ገቢ (ሞዴል 19) ፤ የንብረት ወጪ (ሞዴል 22) ስራ በአንድ የግምጃ ቤቱ ባለሙያ የሚከናወን መሆኑ
- በግምጃ ቤቱ ውስጥ አገልግሎት አይሰጡም ተብሎ ተቀመጡ በርካታ ንብረቶች እንደነ ኮምፒተር ብዛታቸዉ 357፣የመኪና መለዋወጫ፣ አሮጌ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች ብዛታቸዉ 433 የሚሆን የመኪና ጎማዎች፣ 35 ኩንታል የምስር ክክ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ

ተሽከርካሪን በተመለከተ

- ልብሬ እና ታሊጋ የሌለዉ ባለበትነቱ የማይታወቅ አራት ትራክተር ለአመታት የቆዩ መሆኑ ፡፡
- በግምጃ ቤቱ እስቶክ የሚያመዛዝን ባለሙያ እና የመለዋዎጫ ዕቃዎችን በዳታ መዝግቦ የሚይዝ /ዳታ ኢንኮደር/ ባለሙያ ያልተሟላ መሆኑ ፤

በረፈራል ሆስፒታል የአላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት

- በአላቂ ንብረት ግምጃ ቤቱ እስቶክ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ፤ የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ና የማመዛዘን ስራ በአንድ ባለሙያ የሚከናወን መሆኑ
- በአላቂ ንብርት ክፍል ውስጥ ቢን ካርድ እና እሰቶክ ካርድ ስርዓት የማይተገበር መሆኑ፡፡

<u>የሪፈራል ሆስፒታል የቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤትን በተመለከት</u>

- የቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት የንብረት ገቢ (ሞዴል 19) ፤ የንብረት ወጪ (ሞዴል 22) ስራ በአንድ የግምጃ ቤቱ ባለሙያ የሚከናወን መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ ውስጥ የህክምና መሳሪያ እንደነ x-ray ማሽን እና dental x-ray ማሽን ከአንድ ዓመት በላይ ሜዳ ላይ ተጥሎ የተቀመጡ መሆኑን እንዲሁም በሆስፒታሉ ግቢ ዉስጥ የቋሚ እስቶር የሌሌ በመሆኑ እቃዎቹ ሜዳ ላይ ተበትነዉ ያሉ መሆኑ፡፡

5.1.2 <u>ስጋት፤</u>

ዩኒቨርሲቲዉ በንብረት አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ተግባራዊ የማያደርግ ከሆነ የዩኒቨርሲቲዉ ንብረት አያያዝ፣ አጠቃቀም፣ አጠባበቅና አመዘጋገብ ለበለጠ ጥፋት ሊጋለጥ ይችላል፡፡ መንግስትንም ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

5.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ ፤</u>

- ለቁጥጥር ያመች ዘንድ በባለሙያ ተለያይተው የሚሰሩ ስራዎች መሰራት አለባቸው፡፡ በመሆኑም እስቶክ የሚያመዛዝን ባለሙያ፣ የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) የሚሰራ ባለሙያ እና የዕቃዎችን መረጃ በኮምፒዩር መዝገቦ የሚይዝ ዳታ ኢንኮደር ባለሙያ ሊኖር ይገባል ፡፡
- የቢን ካርድ አሰራር በተሟላ ሁኔታ መተግበር አለበት፡፡
- የዕቃዎች አቀማመጥ የካይዘንን አሰራር መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡
- የዩኒቨርስቲው ተሽከርካሪዎች፣ የመለዋወጫ ዕቃዎች፣ወንበሮችና ጠረጴዛዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉት እንዲጠገኑ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉት ከመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጋር በመነጋገር በስጦታ እና በሽያጭ የሚወገዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው የንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅ፣ አመዘጋገብ እና አወጋገድ በአዋጁና በመመሪያዉ መሰረት ተግባራዊ የሚደረግበት አሰራር ሊፈጠር ይገባል ፡፡

5.1.4 <u>የሥራ ክፍሉ ምላሽ</u>

በማዕከል አላቂ ዕቃ ግ/ቤት አስመልክቶ የተሰጠን ሃሳብ ስቶክ ገቢ ደረሰኝ(ሞዴል 19)፤ የምብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) እና የማመዛዘን ስራ በአንድ ባለሙያ የሚከናወን ነው የሚለው ላይ የምንሰጠው ሃሳብ ገቢ ደረሰኝ(ሞዴል 19) ገቢ የሚያደርገው የቋሚ ዕቃዎች ዕቃ ግምጃ ቤት ሃላፊ ሲሆን ሌሎች የዕቃ ግምጃ ቤት ሃላፊዎች ደግሞ ከቋሚ ዕቃዎች ዕቃ ግምጃ ቤት ሃላፊ ወጪ በማድረግ የዕቃዎችን ገቢና ወጪ እንዲሁም

የማመዛዘን ስራ የሚሰሩ ሲሆን የተሰጠን ሃሳብ ከወትሮ አሰራራችን የተለየና አዲስ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት እንደገና ችግሩን ፈትሸን ተግባራዊ የምናደርግ ይሆናል፡፡ በቋሚ ዕቃ ግ/ቤታችን ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ንብረቶች እንደ ኮምፒዩተር ብዛት 357፤ የመኪና መለዋወጫዎች፤ አሮጌ ወንበሮችና ጠረንጴዛዎች፤ ብዛት 433 የሚሆን የመኪና ጎማዎች፤ 35 ኩንታል ምስር ክክ ተከማችተው እንደሚገኙ ተገልጧል፡፡ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን በተመለከተ የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ከሚያዝያ 4-8/2013 ዓ.ም የተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች፤ ፈርኒቸሮች፤ ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶችና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችንመረጃ መዝግበን እንድንልክላቸው በጠየቁን መሰረት የላክንላቸው ሲሆን እንደገና በደብዳቤ ቁጥር መግኤ/ሰ-2/9/58 በቀን 19/9/2013 ዓ.ም በፃፉት መሰረት በእነዚህ የተመዘገቡ ንብረቶች አወጋገድ ዙሪያ የመንግስት ውሳኔ እስከሚሰጥባቸው ድረስ ባሉበት ሁኔታ እንዲቆዩ ያሳሰቡን በመሆኑ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎቹ ተመዝግበውና ተለይተው ያሉ ሲሆን ለጊዜው ከኤጀንሲው አቅጣጫ እየተጠባበቅን እንገኛለን፡፡

የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨረሱና ከሾፌሮች እጅ ወደ ዕቃ ግምጃ ቤት ተመላሽ የተደረጉ የተለያዩ ጎማዎች ለይተን መረጃቸውን በማጠናከር በህጉና መመሪያው በሚያዘው መሰረት እንዲወገድ ለሚመለከተው አካል በማስተላለፍ ውሳኔ እየተጠባበቅን እንገኛለን፡፡

በተማሪዎች አገልግሎት ማዕከል 35 ኩንታል የምስር ክክ ተከማችተው ይገኛሉ የተባለው የተበላሸና እንዲወገድ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ቀርቦ የተወሰነ ሲሆን በውሳኔው መሰረት የሚወገድ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም አሮጌ ወንበሮችና ጠረንጴዛዎች ከማይፈለግበት የስራ ክፍሎች ወደ ዕቃ ግምጃ ቤት የተመለሱ ቢሆንም በአንዳንድ የስራ ክፍሎች ዘንድ ለስራ የሚፈለጉና አውጥተው እየተጠቀሙ ስለሆነ ዕጥረት እንዳይከሰት ለጊዜው የተወሰኑ ወንበሮችና ጠረንጴዛዎችን ለማስቀመጥ ችለናል፡፡

በቱቺንግና ሪፈራል ሆስፒታል በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የህክምና መሳሪያ እንደነ X-Ray Machine እና Dental X-Ray Machine ሜዳ ላይ ተጥሎ እንደተቀመጠ የተገለፀ ሲሆን ማሽኖቹ የመጡት በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት በመሆኑና ማሽኑን የሚገጣጥሙበት ክፍል በኮቪድ ህመምተኞች በመያዙ ለጊዜው ያለቦታው እንዲቀመጥ የተደረገ ሲሆን የሆስፒታሉን የክፍሎች ጥበት ለመቅረፍም ዩኒቨርሲቲው በግንባታ ላይ በመሆኑ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ችግሩ የሚፈታ ይሆናል፡፡

ተሸከርካሪን በተመለከተ ሊብሬና ታርጋ የሌለው ባለቤትነቱ የማይታወቅ አራት ትራክተር አለ ስለተባለው ትራክተሮቹ በተገዙበት ወቅት ኢንዱስትሪው ከውጪ ሀገር የትራክተር ዕቃዎችን አስመጥቶ የሚያመርትና ተያያዥ ዶክመንቶች እንዳልደረሳቸውና ለጊዜው ሰሌዳ ለማውጣት እንደሚቸገር ነገር ግን ታርጋው እስከሚወጣ ድረስ ለእርሻ ስራ እንድንጠቀም ለሚመለከተው አካል መልካም ትብብር እንዲያደርጉልን ደብዳቤ ጠፃፉልን ሲሆን በዩኒቨርሲቲያችን ደረጃም ሊብሬና ታርጋ ለማውጣት እያደረግን ያለውጥረት እስከ አሁን በሂደት ላይ በመሆኑ ለወደፊትም ችግሩን ለመፍታት የምንሰራ ይሆናል፡፡

የሪፈራል ሆስፒታል የቋሚ ዕቃዎችና አላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤትን በተመለከተ ከዚህ በፊት በአንድ ባለሙያ ብቻ የንብረት ገቢና ወጪ ሲሰራ የነበረው በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ተስተካክሎ እየተሰራ በት መሆኑን እንገልፃለን፡፡

በግምጃ ቤቱ ውስጥ የህክምና መሳሪያ እንደነ X-Ray Machine እና Dental X-Ray Machine ከአንድ ዓመት በላይ ሜዳ ላይ ተጥሎ ተቀምጧል ለተባለው ዕቃው ሜዳ ላይ ሳይሆን በሆስፒታሉ ቤት ውስጥ የተቀመጠ ሲሆን ግሽኑ ግን በውጪ ባለሙያዎች የሚተከል ሲሆን በአሁኑ ወቅት በአካባቢያችን ባለው የፀጥታ ስጋት ምክንያት ባለሙያዎችን አግኝተን ማስተከል ያልቻልን መሆናችንን እንገልፃለን፡፡

6 <u>ሌሎች ጉዳዮች፣</u>

6.1 <u>እርምጃ የተወሰደባቸውና ያልተወሰደባቸው ያለፈው በጀት ዓመታት ኦዲት ግኝቶች፤</u>

6.1.1 <u>ግኝት፤</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰረት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን እርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸው እና የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው በተገለፀው መሰረት ለዩኒቨርሲተው በ 2012 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ ለማጣራት ኦዲት ሲከናወን፤

* በ2011 በጀት አመት ኦዲት ዩኒቨርሲቲው የተጋባዥ መምህራን ክፍያ በአዋጁ መሰረት 30% መቀነስ ሲገባው አለአግባብ 2% የቀነሰ በመሆኑ በኦዲት ናሙናችን መሠረት ዩኒቨርሲቲው ከተጋባዥ መምህራን ክፍያ ላይ በመመሪያ መሠረት ስለመቀነሱ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከተከፈለው ክፍያ ላይ ብር 22,176.00 የሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

6.1.2 ሥጋት፣

ዩኒቨርሲቲው ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ መፈጸም ለገንዘብ ብክነት ከመዳረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

6.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ያልተሰበሰበው የመንግሥት ግብር ተሰብስቦ ለሚመለከተው መ/ቤት ገቢ እንዲደረግና ለወደፊቱም የመንግስት ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ሥራዎችን ማከናወን ይገባል፡፡

6.1.4 የሥራ ክፍሉ ምላሽ፣

በ2011 በጀት ዓመት ግኝት ላይ ክትትል አስመልክቶ በጊዜው በበጀት ዓመቱ ለተጋባዥ መምህር ክፍያ ሲከፈል 30% መቆረጥ ሲገባው 2% የተቆረጠ በመሆኑ ተመላሽ እንዲደረግ እንደግኝት ቢቀርብም በጊዜው የወጣው መመሪያ ያልደረሰን ሲሆን ገንዘቡን ተመላሽ ለማስደረግ ግለሰቦቹን ማግኘት ያልቻልን በመሆኑ እና በአሁኑ ጊዜ በመመሪያው መሰረት ተስተካክሎ እየተሰራ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

አባሪ 1 አቅራቢዎች በውላቸው መሰረት ባለማቅረባቸው ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ ዝርዝር

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከ.ያ ቁጥር	የእቃው አይነት	የድርጅቱ ስም	የውሉ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን	በውሉ መሰረት ዕቃ ማስረከቢ.ያ የመጨረሻ ቀን	ዕቃው ገቢ የሆነበት ቀን	ዕቃው የዘገየበት ቀን ብዛት	የጉዳት ካሳው መጠን
1	25/02/13	807212	Orthopedics traction Bed ዕቃዎች ግዥ	ቲቲዋይ የመድሀኒት ሀክምና መሳሪያዎች አስመጪ ድርጅት	1,380,000.00	20/10/2012	04/02/13	118 ቀናት	138,000.00 /10%/
2	25/02/13	807211	የሀክምና ዕቃዎች ግዥ	እዮብ አለማየሁ ሀክምና መሳሪያዎች አስመጪ ድርጅት	676,311.00	20/10/2012	24/02/13	138 ቀናት	67,631.1 /10%/
							ድምር		205,631.1

አባሪ 2 የ5061 ተቀጽላ ሌከር ኮድ ያልተሰጣቸው ተቋራጮች

	Contractor's Name	Code	Amount from Your report
1	Ababo Kese		65,595.63
2	Abate Tadese		52,346.98
3	Abera,Taressa & Dula con		9,141.15
4	Abinet Wube GC		105,307.55
5	Amare Helen & Sintayehu		67,673.36
6	Bernabas Const.SME		634.05
7	Bekele Cobil StoSME		4,955.54
8	Burka Eba con.SME		21,632.91
9	Chala Kena GC		524,239.89
10	Desalegn Alemayehu GC		76,317.88
11	Ebisa Milkessa & Tsagaye		11,344.56
12	Ercon construction PLC		72,312.82
13	Estifanos & Yohanis SME		50,910.00
14	FE construction PLC		259,933.40
15	Fekadu Bekele GC		60,613.74
16	Filate construction		48,975.51
17	Fituma tefera GC		13,120.38
18	Flintstones Eng		909,903.35
19	GBY const SME		9,366.80
20	G2 metal &wood work		33,910.01
21	Gemta construction SME		12,389.05
22	Habtamu, Temesgen & Dawit		37,818.33
23	Henok & Getinetwood & Metal		56,857.40
24	Isayas Alemu wood work		12,130.24
25	Generef cobblestone SME		53,782.50
26	Jitu kese SME		13,181.11
27	Keraj cobblestone SME		49,622.58
28	Komto cobblestone SME		23,003.85
29	M- construction		189,550.13
30	Merga Nuru GC		19,691.70
31	Milkesa , Ebisa & Tesfaye		42,176.06
32	Nule GC		30,247.30
33	NY Engineering PLC		617,311.29

34	Olbirat Engineering PLC		11,690.59
35	Shiferaw & Aschalew		90,748.88
36	Tegegn Tadese GC		8,520.84
37	Temesgen Tesfa GC		3,094.66
38	Wagari & Frians ,Fayisa		29,943.71
39	Walfure coblstone		180,635.04
40	Waluman construction		11,234.14
41	Yonan Biniam & Ayana SME		47,466.15
42	Yosef Oljira Works SME		8,271.83
43	Zenebe3ch Sura Work		12,760.82
44	Bahilu,Wakene BC & friends		155,226.05
45	Friends		28,286.71
46	Megersa ,Hawi & friends		118,858.76
47	Shambu campus		24,645.03
48	Hebron construction		1,316,244.69
			5,603,624.95

አባሪ 3 ያለገቢያ ጥናት የተፈጸመ ግዥ

ተ/ቁ	ቀን	ቫውቸር ቁጥር	የደረሰኝ አይነት	የተከፈለው ድርጅት	የተገዛበት የብር መጠን
1	26/02/2013	458558	PV	ለምርክ ሾፕ የተገዛ እቃ	17,288.00
2	12/02/2013	807293	PV	ለምርክ ሾፕ የተገዛ እቃ	195,173.75
3	26/01/2013	807274	PV	ለምርክ ሾፕ የተገዛ እቃ	139,496.00
4	12/02/2013	807292	PV	ለምርክ ሾፕ የተገዛ እቃ	191,750.00
5	06/04/2013	458751	PV	ለምርክ ሾፕ የተገዛ እቃ	83,000.00
6	10/06/2013	85477	PV	ለምርክ ሾፕ የተገዛ እቃ	145,969.04
					772,676.79

ተ/ቁ	ቀን	ቫውቸር ቁጥር	የተገዛው ዕቃ	የተገዛበት የብር መጠን
1	08/07/2013	458996	ለምርክ ሾፕ ዕቃ	195,633.53
2	07/05/2013	458712	ለምርክ ሾፕ ዕቃ	197,719.45
3	18/09/2013	85296	ለምርክ ሾፕ ዕቃ	194,496.70
			ድምር	587,849.68

አባሪ 5 የበጀት አጠቃቀም

ከተፈቀደው በጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ				
ከመደበኛ በጀት ከበጀት በላይ የወጣ				
የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ከበጀት በላይ የወጣ	በመቶኛ
6114	43,239,700.00	43,768062.13	528,362.13	1
6115	101,200,000.00	108,287,662.15	7,087,662.15	7
6116	51,695,700.00	58,427,471.95	6,731,771.96	13
6214	16,509,900.00	18,554,549.94	2,044,649.94	12
6221	509,200.00	532,933.12	23,733.12	5
6222	378,000.00	895,890.37	517,890.37	137
6216	98,511,600.00	128,195,456.81	29,683,856.81	30
6231	86,544,916.67	94,701,538.85	8,156,622.18	9
6241	18,356,200.00	19,342,170.86	985,970.86	5
6244	18,974,500.00	21,148,120.91	2,173,620.91	11

6253	3,551,949.00	3,628,295.85	76,346.85	2
6255	3,492,000.00	4,040,947.70	548,947.70	16
	442,963,665.67	**501,523,100.64**	**58,559,434.98**	
ከካፒታል በጀት ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ				
6326	16,000,000.00	19,439,602.34	3,439,602.34	21
	16,000,000.00	**19,439,602.34**	**3,439,602.34**	
ከተስተካከለው በጀት ከ10 በላይ ስራ ላይ ያልዋለ በጀት				
ከመደበኛ በጀት ያልተሰራበት				
የሂሳብ መደብ	**የተስተካከለ በጀት**	**ሥራ ላይ የዋለ**	**ያልተሰራበት**	**በመቶኛ**
6133	1,441,200.00	906,689.22	534,510.78	37
6212	16,572,200.00	13,284,867.06	3,287,332.94	20
6213	5,120,000.00	1,926,799.63	3,193,200.37	62
6215	34,740,900.00	24,071,406.90	10,669,493.1	31
6217	15,654,400.00	13,835,358.89	1,819,041.11	12
6218	21,847,800.00	17,760,626.64	4,087,173.36	19
6219	1,178,000.00	693,434.99	484,565.01	41
6223	8,139,500.00	7,326,305.58	813,194.42	10
6232	10,405,300.00	7,175,272.01	3,230,027.99	31
6233	12,576,800.00	11,160,936.07	1,415,863.93	11
6243	1,444,000.00	223,504.47	1,220,495.53	85
6251	3,306,500.00	2,268,740.92	1,037,759.08	31
6254	3,135,000.00	2,830,072.39	304,927.61	10
6256	3,069,983.33	2,277,678.24	792,305.09	26
6257	6,010,000.00	5,300,821.42	709,178.58	12
6271	483,700.00	348,594.00	135,106.00	28
6412	6,500,000.00	4,004,975.00	2,495,025.00	38
6419	98,087,000.00	79,765,610.83	18,321,389.17	19
	303,525,963.33	**245,478,299.32**	**54,550,589.07**	

ከካፒታል በጀት ያልተሠራበት በጀት				
6313	74,975,900.00	21,446,907.36	53,528,992.64	71
6314	9,000,000.00	4,759,489.99	4,240,510.01	47
6321	2,000,000.00	6,561.00	1,993,439.00	100
ድምር	**585,075,900.00**	**403,796,706.94**	**59,762,941.65**	
ከውስጥ ገቢ ከተደለደለው በጀት ያልተሠራበት				
የሂሳብ መደብ	**የተስተካከለ በጀት**	**ሥራ ላይ የዋለ**	**ሥራ ላይ ያልዋለ**	**በመቶኛ**
6113	550,000.00	-	550,000.00	100
6114	5,535,900.00	146,886.00	5,389,014.00	97
6133	254,000.00	-	254,000.00	100
6212	1,550,000.00	5,960.00	1,544,040.00	100
6213	691,100.00	2,568.00	688,532.00	100
6214	138,600.00	4,300.00	134,300.00	97
6215	299,700.00		299,700.00	100
6217	1,413,300.00	12,804.80	1,400,495.20	99
6218	255,000.00		255,000.00	100
6221	42,900.00	1,608.00	41,292.00	96
6223	208,000.00		208,000.00	100
6231	13,820,600.00	9,745,753.92	4,074,846.08	29
6232	1,680,000.00	818,658.85	861,341.15	51
6233	1,387,500.00	579,416.14	808,083.86	58
6241	20,200.00	2,020.00	18,180.00	90
6251	300,000.00		300,000.00	100
6252	3,880,900.00	3,013,080.00	867,820.00	22

6253	100,000.00		100,000.00	100
6255	531,100.00		531,100.00	100
6256	723,100.00	422.00	722,678.00	100
6257	50,000.00		50,000.00	100
6258	50,000.00		50,000.00	100
6259	50,000.00		50,000.00	100
6271	100,000.00		100,000.00	100
6313	208,800.00		208,800.00	100
	33,840,700	**33840700**	**19,507,222.29**	